Digital Ethiopia
ዲጂታል ኢትዮጵያ

# የዲጂታል መንግስት ስትራቲጂ እና የኤሌክትሮኒክ ንግድ ስትራቴጂ አጭር ማብራሪያ

Digital Ethiopia

ዲጂታል ኢትዮጵያ

# የዲጂታል መንግስት ስትራቴጂ እና የኤሌክትሮኒክ ንግድ ስትራቴጂ አጭር ማብራሪያ

የኢትዮጵያ መንግሥት የዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የኢኮኖሚ እድገትን ለማምጣት እንዲሁም የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥን እና የዜጎችን ህይወት ለማሻሻል በቁርጠኝነት እየሰራ ይገኛል። በዚህም መሠረት መንግስት በርካታ ጥረቶችን እያደረገ ሲሆን የዚሁ ጥረት አካል የሆኑትን የዲጂታል መንግስት ስትራቴጂ እና የኤሌክትሮኒክ ንግድ ስትራቴጂ ስትራቴጂዎች አዘጋጅቶ ወደተግባር ለማስገባት ዝግጅት እየደረገ ይገኛል። እነዚህ ስትራቴጂዎች የኢትዮጵያን የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ጉዞ ውስጥ የመንግስት አገልግሎቶች ዲጂታይዜሽን ላይ እና በኤሌክትሮኒክ ንግድ ልማት ላይ አቅጣጫ የሚያስቀምጡ እና አገሪቱ የዲጂታል ኢኮኖሚን ትሩፋቶች በሙሉ አቅም እንድትጠቀም የሚያግዙ ናቸው።

የኢትዮጵያ መንግሥት ዲጂታል ቴክኖሎጂዎች ዋነኛ የለውጥ (ትራንስፎርሜሽን) ኃይል መሆናቸውን በመገንዘብ ለዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ቅድሚያ ሰጥቷል። ለዘርፉ የተሰጠው ትኩረትም የዲጂታል መሠረተ ልማትን ለማስፋት፣ ዲጂታል ዕውቀትን ለማስፈን እና ለዲጂታል ፈጠራ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ባለሙ የተለያዩ የመንግሥት ፕሮጀክቶች እና ፖሊሲዎች ውስጥ ተንጸባርቋል። የዲጂታል መንግስት እና የኤሌክትሮኒክ ንግድ ስትራቴጂዎች የዚህ ሰፊ ራዕይ ቁልፍ አካላት ሲሆኑ ዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን ሥራ ላይ ለማዋል እና የልማት ግቦቹን ለማሳካት መንግሥት ያለውን ቁርጠኝነት ያሳያሉ።

የዲጂታል መንግስት ስትራቴጂ የመንግሥት አገልግሎቶችን በማዘመን እና ዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥን በማሻሻል ላይ ያተኩራል። ስትራቴጂው ይበልጥ ቀልጣፋ፣ ግልጽነት የተላበሰ እና ዜጋን ያማከለ ሕዝቡን በተሻለ መልኩ የሚያገለግል መንግሥት ለመፍጠር ያለመ ነው።

**የኢትዮጵያ የዲጂታል መንግስት ስትራቴጂ (2025-2030) በአራት ምሰሶዎች ላይ የተገነባ ነው።**

1. የዲጂታል መንግስት አንኳሮችን ማበልጸግ (Developing Digital Government Core)
2. የዲጂታል መንግስት መሰረተ ልማቶችን መገንባት(Building Digital Government Foundations)
3. የዲጂታል መንግስት አስቻዮች መተግበር (Implementing Digital Government Enablers)
4. የዲጂታል መንግስት ትግበራ አስፈላጊ ጉዳዮችን ሟሟላት (Ensure Digital Government Essentials)

የስትራቴጂው ዓላማ በዲጂታል የተገናኘ፣ ተጠቃሚን ያማከለ፣ በዳታ ላይ የተመሰረተ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ እና በዲጅታል አሠራሩ የተለወጠ እንዲሁም ለሁሉም ዜጎች እና የንግድ ተቋማት ቀልጣፋና ተመጣጣኝ አገልግሎት የሚሰጥ የመንግሥት የአሰራር ሥርዓት መፍጠር ነው። ስትራቴጂው የኢትዮጵያ መንግስት የመንግሥት የዘርፍ ማሻሻያ አጠቃላይ እቅድ አካል ሆኖ የሚተገበር ነው።



**የዲጂታል መንግስት ስትራቴጂ የሚከተሉት አላማዎች፡-**

* የተቀናጁ፣ ተደራሽ እና ተጠቃሚን ያማከሉ ዲጂታል የመንግሥት መተግበሪያዎችን እና አገልግሎቶችን ማቅረብ፣
* በዲጂታል የተገናኘ መንግሥትን ለመደገፍ ጠንካራ የዲጂታል መሠረተ ልማት መዘርጋት፣
* የዲጂታል መንግሥት አገልግሎቶችን ቅንጅት እና ቁጥጥር ማሳደግ፣
* የዲጂታል ዕውቀት እና ክህሎትን በመንግሥት ሠራተኞች እና በዜጎች ላይ ማስረጽ
* ለዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ደጋፊ የህግ ማዕቀፎች ማዘጋጀት።
* አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ዲጂታል የመንግሥት አገልግሎቶችን መስጠት
* የዲጂታል የፈጠራ ስነ-ምህዳርን መዘርጋት
* አካታች የዲጂታል ሥርዓትን መዘርጋት
* ዲጂታል የመንግሥት አገልግሎቶችን ደህንነት መጠበቅ እና ከደህንነት ስጋት ነጻ መሆናቸውን ማረጋገጥ።
* የአስተዳደር እና የአሠራር ማሻሻያዎችን መደገፍ
* ቀጠናዊ እና ዓለም አቀፋዊ የዲጂታል ትስስሮችን/ ውህደቶችን ማፋጠን።

**የዲጂታል መንግስት ስትራቴጂ የሚከተሉት ዋና ዋና ክፍሎች፡-**

* አፕሊኬሽኖች እና አገልግሎቶች፡- ስትራቴጂው በመንግስት አካላት የሚሠሩ የኤሌክትሮኒክ አገልግሎቶች ልማትን የሚቆጣጠር እና የሚያስተባብር የዲጂታል መንግሥት ድጋፍ ማዕከል (DGSC) ማቋቋምን ጨምሮ ተጠቃሚን ያማከለ የኤሌክትሮኒክ አገልግሎቶች ልማት እና ትግበራን በቀዳሚ ተግባርነት ያስቀምጣል።
* ዲጂታል መሠረተ ልማት፡- ስትራቴጂው የሀገሪቱን የዲጂታል መሠረተ ልማት ማዘመን እና ማሻሻልን በተለይም የዳታ ማዕከላትን፣ የክላውድ ኮምፒዩቲንግ አቅምን እና የመንግሥት ዋይድ ኤሪያ ኔትወርክን (ጂዋን)ን አስፈላጊነት አጽንኦት ይሰጣል።
* የዳታ አስተዳደር እና ማጋራት፡- ስትራቴጂው በዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ውስጥ የዳታ /ውሂብን/ አስፈላጊነት በመገንዘብ በመንግስት አካላት የዳታ /ውሂብ/ አያያዝን፣ አስተዳደርን እና መጋራትን ለማሳለጥ ዕቅዶችን ዘርዝሯል። ይህም ኮር ዳታቤዞችን ማልማት፣ የዳታ /ውሂብ/ ቁጥጥር ማዕቀፍ ማዘጋጀት እና ውሂብን ግልጽ ማድረግ (Open Data) መቻልን ይጨምራል።
* አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች፡- ስትራቴጂው እንደ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ (AI)፣ ብሎክቼይን እና ኢንተርኔት ኦፍ ቲንግስ (IoT) ያሉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ለውጥ የመፍጠር አቅምን ዕውቅና ይሰጣል። እነዚህን ቴክኖሎጂዎች በመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ ውስጥ ጥቅም ላይ ማዋልን የሚያበረታቱ አገር አቀፍ ስትራቴጂዎች እና ሕጋዊ ማዕቀፎች እንዲዘጋጁ ሀሳብ ያቀርባል።
* ዲጂታል ስነ-ምህዳር፡- ስትራቴጂው የትብብርን አስፈላጊነት የሚያጎላ ሲሆን የግሉ ሴክተርን በማሳደግ፣ ጀማሪ የንግድ ተቋማትን በማስተዋወቅ እና ከአካዳሚክ እና የምርምር ተቋማት ጋር ትብብርን በማጎልበት የዲጂታል ስነ-ምህዳሩን ለማጠናከር ያለመ ነው።
* አስቻዮች፡- ስትራቴጂው የመንግሥት-አጠቃላይ (Whole of Government) የቁጥጥር ማዕቀፍን፣ የዲጂታል ክህሎትና ባህልን ማዳበር፣ ጠንካራ የህግ ማዕቀፍ መዘርጋት፣ የሳይበር ደህንነትን እና የሥራ አለመቆራረጥን (Business Continuity) ጨምሮ ስኬታማ ዲጂታል ትራንስፎርሜሽንን ለማምጣት ቁልፍ አስቻዮችን ይለያል።
* ፋይናንስ፡- ስትራቴጂው ለዲጂታል መንግሥት ልማት ዘላቂ የገንዘብ ድጋፍ አስፈላጊነትን አጽንዖት ይሰጣል። ለዚህም የሀገር ውስጥ የገንዘብ ድጋፍ፣ የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ አጋርነት እና የልማት ድጋፎችን /ዕርዳታ/ በማጣመር ሀብት የማሰባሰብ ተግባራት እንዲከናወኑ ሃሳብ ያቀርባል።

**የዲጂታል መንግሥት ስትራቴጂ የሚከተሉት ቁልፍ መርሆዎች፡-**

* በዲጂታል የተገናኘ መንግሥት፡- በመንግስት አፕሊኬሽኖች እና አገልግሎቶች መካከል ትስስርን ለመፍጠር ውሂብን እንደገና ጥቅም ላይ ማዋልን፣ የጋራ አርክቴክቸርን እና ስታንዳርዶች መጠቀምን ማበረታታት።
* ተጠቃሚን ያማከለ መንግሥት፡- ተደራሽ፣ ቀልጣፋ እና ለተጠቃሚዎች ተስማሚ የሆኑ የዜጎችን፣ የንግድ ድርጅቶችን እና የመንግሥት ሠራተኞችን ፍላጎቶች ያማከሉ አገልግሎቶችን መስጠት።
* በመረጃ (ውሂብ) የሚመራ መንግሥት፡- ውሂብን መሰብሰብ፣ ማደራጀት እና ማጋራት የአገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል፣ ውሳኔ

አሰጣጥን ለመደገፍ እና ፈጠራን ለማበረታታት።

* ደህንነቱ የተጠበቀ መንግስት፡- ደህንነቱ የተጠበቀ ዲጂታል ከባቢን መጠበቅ እና የሳይበር ስጋቶችን ለመከላከል ዕቅዶችን መተግበር።
* ዘላቂ የአካባቢ ጥበቃን የተገበረ መንግሥት፡- የዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን የአካባቢ ጥበቃን ታሳቢ በማድረግ ኃላፊነት በተሞላበት መንገድ መጠቀምን ማበረታታት።

የኢትዮጵያ መንግሥት ይህንን የዲጂታል መንግሥት ስትራቴጂ በተሳካ ሁኔታ መተግበሩ የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥን እንደሚያሳድግ፣ የኢኮኖሚ እድገትን እንደሚያመጣ እና የዜጎችን ህይወት እንደሚያሻሽል ያምናል።

የኤሌክትሮኒክ ንግድ ስትራቴጂ ዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን፣ ፈጠራ የታከለባቸው የንግድ ሞዴሎችን እና አዳዲስ የገበያ አዝማሚያዎችን በመጠቀም ተወዳዳሪ እና የበለጸገ የሀገር ውስጥ እና ዓለም አቀፍ የኤሌክትሮኒክ ንግድ ገበያን በኢትዮጵያ ለመፍጠር ያለመ ነው። ስትራቴጂው ኢኮኖሚውን ለማዘመን እና የኢኮኖሚ እድገትን እና ብዝሃነትን ለማስፋት የታለመ የሰፊው የመንግሥት የዘርፍ ማሻሻያ ጥረቶች ወሳኝ አካል ነው። ስትራቴጂው በኢትዮጵያ ያለውን የኤሌክትሮኒክስ ግብይት ፈጣን ለውጥ እና አቅም በመገንዘብ ለኤሌክትሮኒክ ግብይት ዕድገት እንቅፋት የሆኑትን ተግዳሮቶች በመለየት እና በማሻሻል ላይ መሠረት ያደረገ ነው።



**የኢኮሜርስ ስትራቴጂ የሚከተሉትን ዓላማዎች ያካትታል**

* የፖሊሲ እና የሬጉላቶሪ ምርጥ ተሞክሮዎችን እና የቁጥጥር ሥርዓትን መተግበር።
* ሸማቾች በኤሌክትሮኒክ ግብይት ላይ ያላቸውን ግንዛቤ፣ መተማመን እና እርግጠኝነት ማሳደግ።
* በኤሌክትሮኒክ ንግድ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎን ማሳደግ።
* በኤሌክትሮኒክ ንግድ የወጪ ንግድን ማበረታታት እና የ ውጪ ምንዛሬ ገቢን ማሳደግ።

**የኢኮሜርስ ስትራቴጂው የሚከተለት ዋና ዋና ክፍሎች፡-**

* የህግ እና የቁጥጥር ማዕቀፎች፡ ስትራቴጂው ኤሌክትሮኒክ ንግድን የሚደግፍ ከባቢን ለመፍጠር የህግ እና የቁጥጥር ማዕቀፎችን ለማዘጋጀት እና ለማሻሻል ቅድሚያ ይሰጣል። ይህም አሁን ባሉት ህጎች ላይ ያሉ ክፍተቶችን መፍታትን፣ ለኤሌክትሮኒክ ንግድ ኦፕሬተሮች የንግድ እና የንግድ ምዝገባ ሂደቶችን ግልጽ ማድረግን እና በኦንላይን ግብይቶች ላይ የሸማቾች ጥበቃን ማረጋገጥን ያጠቃልላል።
* ዲጂታል ፕላትፎርሞች፡- ስትራቴጂው ከተጠቃሚው ምቾት፣ ደህንነት እና ተናባቢነት ጋር የተያያዙ ችግሮችን መፍታትን ጨምሮ የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርሞችን ጥራት እና ተደራሽነት ለማሳደግ ዕቅዶችን ይዘረዝራል። ከዚህ ባሻገር የኦንላይን ግብይትን የሚያሳልጥ እና የኢትዮጵያን ምርቶችን የሚያሻሽጥ ብሔራዊ የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም እንዲዘጋጅም ሃሳብ አቅርቧል።
* ዲጂታል ክፍያዎች፡- ስትራቴጂው የኤሌክትሮኒክ ንግድ ግብይቶችን የሚደግፍ ጠንካራ የዲጂታል ክፍያዎች ስነ-ምህዳርን

ለመፍጠር ያለመ ነው። ይህም ከተናባቢነት፣ ከደህንነት እና ከፋይናንሺያል አካታችነት ጋር የተያያዙ ተግዳሮቶችን መፍታትን ያካትታል። ይህ ስትራቴጂ በጥሬ ገንዘብ ላይ ጥገኛነትን ለመቀነስ እና የኦንላይን ግብይቶችን ለማሳደግ የዲጂታል ክፍያ ሥርዓቶችን መጠቀምን ያበረታታል።

* ሎጂስቲክስና አቅርቦት አገልግሎት፡- ቀልጣፋ ሎጅስቲክስ ለኤሌክትሮኒክ ንግድ ያለውን አስፈላጊነት በመገንዘብ ስትራቴጂው የትራንስፖርት ኔትዎርኮችን ለማሻሻል፣ ከአቅርቦት (Delivery) እና የኦንላይን ግብይት ትዕዛዝን ከመፈጸም (Fulfillment) ጋር የተያያዙ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ እና የመጨረሻ ማይል አቅርቦትን የሚያስችል ብሄራዊ የአድራሻ ሥርዓት ለመዘርጋት ዕቅዶችን አውጥቷል።
* አቅም ግንባታ፡- ስትራቴጂው በዜጎች፣ በንግድ ተቋማት እና በመንግሥት ሠራተኞች ውስጥ የዲጂታል ክህሎት እና የኤሌክትሮኒክ ንግድ አቅምን ማዳበር ያለውን ጠቀሜታ ያሳያል። በተጨማሪም የኤሌክትሮኒክ ንግድን በስፋት ጥቅም ላይ ለማዋል እና በዲጂታል ኢኮኖሚ ውስጥ ሁሉን አቀፍ ተሳትፎን ለማረጋገጥ የተለያዩ የስልጠና እና የድጋፍ ፕሮግራሞችን አካቷል።

**ስትራቴጂው የዘርፉን ቁልፍ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ እና የኤሌክትሮኒክ ንግድ እድገትን ለማስፋት አራት ዋና ዋና ፕሮጀክቶችን አካቷል፡**

* የኤሌክትሮኒክ ንግድ ሬጉላቶሪ ሳንድቦክስ፡- የንግድ ምዝገባን፣ ፍቃድ አሰጣጥን እና የግብር አሰባሰብን ጨምሮ ለኤሌክትሮኒክ ንግድ ቁጥጥር አዳዲስ ሬጉላቶሪ አካሄዶችን ለመፈተሽ እና ለመተግበር።



* አገራዊ የኤሌክትሮኒክ ንግድ ቋት፡- ሀገር በቀል የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርሞችን ለማሳደግ እና ደንበኞች የምርቶች እና አገልግሎቶች መረጃ በተማከለ መልኩ እንዲያገኙ ማስቻል።
* የገጠር ኢኮሜርስ ማስፋፊያ፡- በገጠራማ አካባቢዎች ኢኮሜርስ እንዲስፋፋ በማድረግ የገጠሩን ማህበረሰብ በቀጥታ የሚሳትፍበትን ስረአት መፍጠር

የዲጂታል መንግሥት እና የኤሌክትሮኒክ ንግድ ስትራቴጂዎች በኢትዮጵያ የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ጉዞ ውስጥ ወሳኝ እርምጃዎች ናቸው። መንግሥት የዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን በመተግበር አገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል፣ የኢኮኖሚ እድገትን ማረጋገጥ እና የበለጠ አሳታፊ እና የበለፀገ ማህበረሰብ መፍጠር ያስችላሉ ብሎ ያምናል። እነዚህን ስትራቴጂዎች በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ በሁሉም ደረጃ የሚገኙ የመንግስት ተቋማት፣ የግሉ ዘርፍ፣ የሲቪክ ማህበራት እና ዜጎችን ጨምሮ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ትብብር እና ቁርጠኝነት ይጠይቃል።

Digital Ethiopia
ዲጂታል ኢትዮጵያ